# <u>የሐዘን መግለጫ</u>

# <u>የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር-በታላቅዋ ብሪታንያ</u>

የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር — በታላቅዋ ብሪታንያ — በክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ዜና ዕረፍት ጥልቅ ሐዘን የተሰማው መሆኑን ይገልፃል። ክብር ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ የሃገራችን ብሔር ፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብትና እኩለነት ሳይሸራረፍ በሕገ፥መንግስቱ እንዲከበር ፤ሕዝቦች በመፈቃቀድ ፤ በመከባበርና ተቻችለው በመኖር ዋና ጠላታችን የሆነውን ድህነት ታሪክ ለማድርግ ቆርጠን እንድንነሳሳ ያመላከቱን ታላቅ ራዕይ ያነገቡ በሳል መሪ ነበሩ።

ክቡር ጠቅላይ ሚኒስተር መለስ ዜናዊ ለብዙ ዘመናት የማይደፈር መስሎ ሲታይ የነበረውን አባይን የመገደብ የኢትዮጵያዊያን የረጂም ጊዜ ህልምና ህዳሴ በቆራጥነት ዕውን ለማድረግ የተነሱ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጅ ናቸው።

ከዚህም ሌላ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሃገራችን በልማት ጎዳና እድትጓዝ ያለምንም ዕረፍት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ጊዚያቸውን ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ በማገልገል ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለዋል። እርሳቸው የተለሙትን ከድህነት የመውጣት ራዕይ ከዳር ይደርስ ዘንድ ማህበራችን በቆራጥነት የሚታገል መሆኑን ቃል ይገባል።

የአማራ አቀፍ ልማት ማህበር - በታላቅዋ ብሪታንያ- የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴና መላ አባላቱ የተሰማውን ጥልቅ ሃዘን እየገለፀ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብና ለቤተሰቦቻቸው መጽናናትን እንመኛለን።

## አልማ- በታላቅዋ ብሪታንያ